ታህሳስ 10 ቀን 2011 ዓ.ም

<u>ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 880/881/882 መሠረት የቀረበ የቁም ኑዛዜ</u>

ኑዛዜ አድራጊ ------ ወ/ሮ -------= (ዜግነት ኢትዮጵያዊት)

አድራሻ፡- ________

የኑዛዜ ተቀባይ -------አቶ --------- (ዜግነት ኢትዮጵያዊት)

አድራሻ ፡- ________

እኔ ኑዛዜ አድራጊ በትክክለኛ አእምሮዬ ማንም ሰው ሳያስገድደኝ በራሴ ተነሳሽነት ከዚህ የሚከተለውን የቁም ኑዛዜ እራሴ እየተናገርኩ በኮምፒውተር ቃሌ ተጽፎ በትክክል መሆኑን በምስክሮቼ ፊት ተነቦልኝ ፈርሜአለሁ።

እኔ ኑዛዜ አድራጊ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን በኦሮሚያ ክልል ሱሉልታ ከተማ ቀበሌ ጎቶ ኖኖ መናአቢቹ ልዩ ስም ዲዲምቱ ማሣ የአንድ ጥማድ በሬ ማሣ የሚሆን ውስጥ የሚገኘውን ንብረቴን አዋሳኞቹ በሰሜን የአቶ ኩባ ቦኪ ለታ፣በደቡብ መንገድ፣በምስራቅ አቶ መገርሳ ሁንዴ ሸኔ፣በምዕራብ የወ/ሮዳዊቱ ደገፋ የሚያዋስነውን ማሳ መሬት ከወንድሞችና ከህቶቹ ጋር ክርክር ውስጥ እንዳይገቡ በኑዛዜ እንዳስቀምጥለት ተገድጃለሁ ይህም የሆነበት ምክንያት ከወንድሙ ጋር ሲያርስልኝ ፣ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ስላገለገለኝ ነው ።

2ኛ/ አሁን የሚኖርበት መኖሪያ መሬት ቦታ የሚያዋስነው በሰሜን አውራ መንገድ፣በደቡብ አቶ ተገኑ እሸቱ ግቢ፣በምስራቅ የወ/ሮ ኩሊ ወርዶፋ ይዞታ፣ በምዕራብ አቶ ናኖ ቶላ ቢፍቱ ግቢ የሆነውን መሬት እንዲጠቀምበትና ያለጠያቂ እንዲገለገልበት ህገና ልጄቹም ጭምር እንዲያውቁት በኑዛዜ መልክ እንዳስቀምጥለት ተገድጃለሁ።ስለሆነም ወድጄና ፈቅጄ ማንም እንዳይነካበት በጋራ ከሚካፈሉት በተለየ መልኩ እንዲጠቀሙበት አድርጊያለሁ። ግን ይህንን የሚጠቀሙበት ከእኔ ሕይወት ፍጻሜ በኋላ ለኑዛዜ ተቀባዮች ለአቶ ጫላ አሰፋ ብሩ እና ለወ/ሮ ደብሪቱ አሰፋ ብሩ እንደፍላጎታቸው ስሙን ወደስማቸው አዛውረው ሸጠው ለውጠው እንዲጠቀሙበት የተናዘዝኩላቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ይህ የቁም ኑዛዜ በ 3 ኮፒ ተጽፎ 1ኛ/ በውልና ማስረጃ መ/ቤት 2ኛው ኮፒ በእኔ በተናዛዥ እጅ ሲቀመጥ በምስክር እጅ በ 3 ኛ እጅ እንዲቀመጥ አድርጌአለሁ።

<u>ይህንን የቁም ኑዛዜ ሳደርግ የነበሩ እማኞች</u>

ኑዛዜ አድራጊ ------ ወ/ሮ -------= (ዜግነት ኢትዮጵያዊት)

አድራሻ፡- ________

የኑዛዜ ተቀባይ -------አቶ --------- (ዜግነት ኢትዮጵያዊት)

አድራሻ ፡- ________

እኛም ስማችን የተጠቀሰው ምስክሮች ኑዛዜ አድራጊ ወ/ሮ ኩሊ ወርዶፋ መስቀሉ ማንም ሰው ሳያስገድዳቸው በራሳቸው ፍላጎት በትክክለኛ አእምሮአቸው ከላይ ለተገለጹት ኑዛዜ ተቀባዮች ከላይ የተገለጸውን ኑዛዜ የተናዘዙና ኑዛዜውም በኮምፒውተር አስጽፈው ተነቦላቸው ቃላቸው መሆኑን አምነውበት ሲፈርሙ አይተንና ሰምተን እኛም በምስክርነት ፈርመናል።

<u>የኑዛዜ አድራጊ ስምና ፊርማ</u>　　　　<u>የምስክሮች ስምና ፊርማ</u>

-------------------------------------　　　　1------------------------------

ወ/ሮ ኩሊ ወርዶፋ መስቀሉ